## <u>የረቡዕ መጋቢት 21 ዓም 1997 ዓም ( የማርች 30 2005)</u>

## <u>የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ</u>

## <u>ሕዝባዊ አመፅ/ ሠላማዊ አመፅ</u>

የዓለምን ሕዝቦች ታሪክ በሚገባ የተከታተለ÷ የታዘበና የተረዳ ተመራማሪ ሁሉ÷ ከሚስማማባቸው በርካታ ክስተቶች አንዱ÷ በዘመናት የሕዝብ አመፅ ከፍተኛውን ቦታ የያዘ መሆኑን ነው:: በደልና ግፍ÷ ስቃይና መከራ÷ ጭቆናም ይሁን የፍትህ-ርትዕ መጓደል ሲኖር÷ ሰብዓዊ ፍጡር ሁሉ ማመፁ የሚያጠያይቅ አይሆንም:: እሳት ከሌለ ጭስ አይኖርም እንደሚባለው÷ በደልና ግፍ ከሌለ አመፅ ሊኖር አይችልም:: በመሆኑም÷ የአመፁ ሁሉ ምንጩና ምክንያቱ÷ ያው ዞሮ ዞሮ በደልና ጭቆና ነው:: ፍትኅ-ርትዕ ካለ÷ ዳኝነት ካልተጓደለ÷ አስተዳደር ከተስተካከለ÷ ሙስና ከሌለ፤ የኢኮኖሚውና የፖለቲካው ሥርዓት የሕዝብን መሠረታዊ ፍላጎት እንዲያረካ ሆኖ ከተዋቀረ÷ ሕዝብ ለአመፅ ብቻ አምፃለሁ በሎ የተነሳበት አጋጣሚ መኖሩን አናስታውስም:: ከሟላ ጎደል፤ ሕዝብ መሠረታዊ ፍላጎቶቹ ከተሟሉለት÷ ቅድሚያ የሚሰጠው÷ ሠላማዊ ሕይወቱን እየመራ ቤተሰቡን መርዳት÷ ኑሮውን ማሻሻል÷ ልጆቹን ማሳደግና መልካም ዜጋ እንዲሆኑ መጣር ነው:: ለአመፅና ለመስዋዕት ሲል ብቻ ጊዜውንና ሕይወቱን የሚገብርበት ቅንጦት አይኖረውም::

ይህን የኅብረተሰብ መሠረታዊ ፍላጎትና ምኞት ባለመረዳት ነው ሁል ጊዜ÷ አምባገነኖች ሕዝብን እየጨቆኑ÷ እየበደሉ÷ ግፍና ስቃይ እያበዙበት ወደ አመፅ ትግል የሚገፋፉት:: አመፅን ለማስወገድ በግድ የጭቆናንና የበደልን ምንጭ ማድረቅ አማራጭ አይኖረውም:: ያ ካልሆነ÷ ሕዝባዊ አመፅ አይቀሬ ነው:: እስካሁን በታሪክ እንደታየው ከሆነ ደግሞ÷ የሕዝብን አመፅ የሚገታው ኃይል አልተገኘም:: ታዲያ÷ መንግሥት የጨበጠ ማነኛውም ኃይል ቢሆን ፤ ማድረግ የሚገባው፤ ሕዝብን ከመበደልና ከመጨቆን መቆጠብ ያለበት መሆኑን ነው:: ሠላምን የሚፈልጉ ሁሉ÷ ሠላም የሚገኝበትንና የሚሰፍንበትን ሁሉ ማድረግ አለባቸው:: ሠላም እንዳይገኝ ምክንያት የሚሆኑትን ክስተቶች ሁሉ÷ በነባቢትም ሆነ በድርጊት መፈፀም የለባቸውም:: ስለ ሠላምና መረጋጋት ጉዳይ÷ ከሕዝብ የበለጠ የሚፈልግና የሚመኝ አይኖርም:: ምክንያቱም÷ሠላም ከሰፈነ÷ ወደ ልማቱ÷ ዕድገቱና ሥልጣኔው ለማተኩር ስለሚያስችለው ነው:: የሠላምን ጥቅምና ማንነት የሚያውቀው ሕዝብ ብቻ ነው:: ይኸም በመሆኑ፤ በየጊዜው ሠላም የሚነሱትን÷ ሁሉ ይቃወማቸዋል:: በሠላማዊ አመፅ! "ዳመናው ሲደምን ይወረዛል ገደል÷ ወተት ይሸፍታል እንኳን ሰው ሲበደል" እያለ ለሕዝባዊ አመፅ ዝግጅት የሚያደርገውም÷ በዚህ መሠረታዊ ምክንያት ነው:: ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ ÷ አመፅ ዕንግዳ አይሆንበትም:: መሳሪያ እያነሳ የውጭ ወራሪ ኃይሎችን በየጊዜው እንደተዋጋቸው ሁሉ÷ የሀገር ውስጥ ጨቋኞችንም÷ በሠላማዊ አመፅ ሲቃወማቸው÷ ሲያስወግዳቸው ኖሯል:: ዛሬም ይሁን ወደፊት ይህንን ከማድረግ የሚያግደው አይኖርም:: ችግሩ ግን÷

ተፈራራቂ አምባገነን ገዥዎቹ ይኸንን ሐቅ መቀበል አለመፈለጋቸው ነው:: ይህን ሐቅ እስካልተቀበሉ ድረስ ደግሞ፥ በሕዝባዊ ኃይልና ትግል መወገዳቸው አይቀርም:: ምን ጊዜም ቢሆን፥ሠላምን ሳይፈልጉ፥ ሠላምን የሚሹ ሁሉ፥ ሠላምን ጭራሽ ሊያገኟት አይችሉምና::

አምባገነኖች፥ እነርሱ ራሳቸው የአመፅ ምንጭ ሆነው እያሉ፥ ብሎም፥ የሠላም አለመገኘትና ያለመረጋጋት ዋነኛ ምክንያቶች ሆነው ሳለ ፥ የሕዝባዊ አመፅ ምክንያት፥ ሌሎች ናቸው በማለት እራሳቸውን ያታልላሉ:: ወደ ሀገር ቤት የሚመጣው የውጭ ዕቃ ዋጋው ሊወደድ የበቃው፥ ኢሕአፓ የሚባለው ድርጅት፥ የሲውዝ ካናልን መተላለፊያ ስለዘጋው ነው ብለው አስቂኝ ቧልት በዘመነ ደርግ እንደደረደሩት ሁሉ፥ የሕዝባዊ-ሠላማዊ አመፅ ምክንያትም ይኸው ድርጅት ሳይሆን አይቀርም በማለት ይቃዣሉ:: ይህን ለማለት ምክንያት አለን:: በአለፈው የካቲት ወር፥ ኢሕአፓ በዴሞክራሲያ ልሳኑ በአወጣው ዕትም ውስጥ የመጭውን የወያኔን ምርጫ አስመልክቶ አቋሙን በማያሻማ መንገድ፥ ለሚታገልለት ለኢትዮጵያ ሕዝብ፥ በመግለጹ፥ የወያኔ መሪዎች፥ ያዙን ልቀቁን ሲሉ እንደባጁ ግልፅ ነበር:: ኢሕአፓ ሕዝቡ እንዲያምፅ በይፋ እየቀሰቀሰ ነው:: በአንድ በኩል በሠላም እታገላለሁ እያለ፥ በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝቡ እንዲያምጽ ይቀሰቀሳል፥ እያሉ የመለስ አገዛዝ ቁንጮዎችና አበጋዞቻቸው ቡራ ከረዮ ሲሉ መሰንበታቸውን የሰማው የኢትዮጵያ ሕዝብ በንቀት ሲስቅባቸው ቆይቷል:: በመጀመሪያ ደረጃ፥ የተጨቆነ፥ የተበደለ፣ የከፋውና የወያኔ ሥርዓት የከረፋው ሕዝብ፥ የማንንም ቅስቀሳና ጉትጎታ የሚያስፈልገው አይደለም:: ለወያኔ መሪዎችም አቤት ወዴት ብሎ ሊገዛላቸው አልቻለም/ አይችልምም:: ይህ አሁን በኢትዮጵያ ያለው የፖለቲካ ሐቅ ነው:: በሁለተኛ ደረጃ፥ ኢሕአፓም ይሁን ሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች፥ በወያኔ አገዛዝ ላይ አምፀው በመታገል ላይ የሚገኙት ወድደው ሳይሆን ተገድድው ነው:: ሕዝቡም በየቦታው የሚያምፀው፥ የወያኔ የዘር ፖሊቲካ ሥርዓት ስለአንገፈገፈው እንጅ ወዶ አይደለም:: የኢትዮጵያ ደሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት አባል ድርጅቶች የጋሪዮሽና የትግል መተከላዊ መርሆአቸው፥ በሕዝባዊ ሠላማዊ አመፅ ወያኔን ከሥልጣን ማስወገድ ነው:: ይህንንም በማድረግ ላይ ናቸው:: ኢሕአፓም በልሳኑም ይሁን በሌሎች መግለጫዎች የሚያወጣቸው ሕዝባዊ ጥሪዎች በሙሉ፥ የኅበረቱን መተከላዊ አቋም የሚያንፀባርቁና የሚያራምዱ ናቸው:: ኢሕአፓ አምባገነኖች ያለ ሕዝባዊና/ ሠላማዊ አመፅ ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው ለሕዝብ ያስረክባሉ የሚል ቅዠትም ይሁን ብዥታ ኖሮት አያውቅም:: ይህንንም ብዥታ የሚያስተናግዱትን ሁሉ፥ ምናልባት ያሳዝኑት እንደሁ እንጅ በዕምነታቸው አያኮርፋቸውም:: በዴሞክራሲ ሂደትና አሰራር ስለሚያምን፥ የሌሎችን የተሳሳተ ዕምነት ባይቀበልም ያከብርላቸዋል:: ኢሕአፓን ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ከሚያስተሳስሩት መሠረታዊ አቋሞቹ መካከል፥ በሕዝባዊ አመፅ አምባገነኖችን አስወግዶ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መተካት አንዱና የመጀመሪያው ነው:: ይህንን ዓይነተኛ የትግል መርሆ በማንገብ ከወያኔ በፊት የነበሩትን ሁለት አምባገነን ሥርዓቶች አይከፍሉ መሥዋዕት እየከፈለ ታግሏቸዋል:: ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን በመሰለፍ! ዘረኛውን የመለስን

ቡድንም እንደዚሁ ከሕዝብ ጎን በመሰለፍ እየታገለው ነው:: የኅብረቱ አባል ሲሆን፥ ግልፅ እንዳደረገው ሁሉ በሕዝባዊ ሠላማዊ አመፅ መንገድም የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እስኪሰፍን አምፆ ይታገላል፥ ያታግላል:: ይህ ደግሞ ምሥጢረ-ወያኔ ሳይሆን፥ የትግላችን ሀሁ የዓላማችን አቡጊዳ ፥ የራዕያችንና ግባችን አልፋና ኦሜጋ ነው:: በእኛ ዕምነት፥ የአምባገነን ሥርዓት፥ ንጉሣዊ ካባም ይጎናፀፍ፥ ወታደራዊ ጃኬት ያጥልቅ፥ ወይም የብሔር ለምድ ይከናነብ፥ ያው ጨቋኝና ሀገር አጥፊ ነው:: የእነ መለስ ጥርቅም የብሔር ድርጅት ነኝ ስላለ ብቻ፥ የተለየ እንክብካቤና እሽሩሩ ሊሰጠው አይገባምውም:: ይህን የሚያስተናግዱ ክፍሎች ካሉ፥ ድግሳቸውን አንካፈልም:: ኢሕአፓ የተመሠረተበት ዓይነተኛ ዓላማና ግብ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ቆሞ፥ አምባገነኖችን ለመታገልና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲሰፍን በሚደረገው ጥረት የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት እንጅ፤ የአምባገነኖችን ላባ ለማናፈስ/ለማራገብ አይደለም:: የመለስ ዜናዊን አገዛዝ ዛሬ አምርሮ የሚታገለው ከዚህ መተከላዊ ዕምነቱ በመነሳት ነው::

ሕዝባዊ ሠላማዊ አመፅን በምንቃኝበት ጊዜ፥ የዚህ የትግል ዓይነት፥ መሥዋዕት አልባ ይሆናል ብለን ራሳችችን በመደለል፤ ሕዝባችንንም ለማታለል አንቃጣም:: የሠላማዊ ትግል፥ ከትጥቅ ትግል ያልተናነሰ ከፍተኛ መሥዋዕትን እንደሚጠይቅ በሚገባ እንረዳለን:: የሰላም ዋጋዋ እጅግ ከፍተኛ ስለሆነም፥ ለሠላም የሚከፈለውም መሥዋዕት የዚያኑ ያህል፤ ከባድና፥ ምናልባትም የህይወት ዋጋ እንደሚከፈልበትም እንገነዘባለን:: የዓለም ታሪክ መመዝገብ ከጀመረ አንስቶ፥ ለሠላም ሲባል ብዙ እጅግ ብዙ መሥዋዕት እንደተከፈለ ሊገነዘብ የማይችለው፥ የሠላምን ዋጋና ክብር የማያውቅ፥ ብሎም፥ በኃይል፥ በአመፅ፥ በሽብርና በጭቆና ሕዝብን ለመግዛት የሚፈልግ ብቻ ነው:: ለዚህ ደግሞ የራሱ የሆነ ምክንያት አለው:: በዴሞክራሲና በሠላም ሀገርን ማስተዳደር ማለት፥ የአምባገነንነት ኃይልና ሥልጣን እየተወገደ፥ የሕዝብን መሠረታዊ መብትና የሥልጣን ልዕልና በሚያስከብር/ በሚያረጋግጥ ሥርዓት ይተካል ማለት ይሆናል:: ይህንን ደግሞ አምባገነን መሪዎች አይፈልጉትም:: የወያኔ መሪዎችም ከዚህ ደዌ ነፃ የሚወጡ አይሆኑም:: ለዚህም ነው ሕዝቡን በጎሳና በክልል ከፋፍለው ሠላም የሚነሱት:: ለዚህም ነው ነፃና ፍትኃዊ ምርጫ እንዲደረግ የማይሹት:: ታዲያ በመሬት ላይ ያለው ሐቅ ይኸ ሆኖ እያለ፥ የመለስ አገዛዝ ቆንጭዎችና አበጋዞቹ ማንኛውንም ጥፋታቸውን ወደ ኢሕአፓ ለማላከክ የሚፍጨረጨሩት በዚህ ምክንያት ነው:: በዚህ ጥረታቸው፥ ሁለት የተለምዶ ስሕተታቸውን ይደጋግሙታል:: አንደኛ እራሳቸውን እያታለሉ ለመኖር የሚያደርጉት ከንቱነት ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ፥ አሁንም፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ የማሰብ ችሎታና የአዕምሮ ብስለት መፈታተናቸው ነው:: በዚህም ተባለ በዚያ፥ ከእነርሱ የዘረኛ አገዛዝ ለመላቀቅ ሕዝቡ ሠላማዊ አመፁን መቀጠሉን ያቆማል ማለት ዘበት ነው:: ገና ምኑ ታየቶ ነው ሀቁ! ይህም፥ ፍትኅ ርትዕ፥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና የሕዝብ ሠላምና መረጋጋት እስከሚሰፍን ድረስ ማለት ነው:: ይኸን የሕዝብ ሠላማዊ አመፅ በመጨረሻ አሸናፊ ሆኖ መውጣት፤ ከራሳችን የየካቲት 66 ተመክሮ ባሻገር ከእነ ማኅትመ ጋንዲ፥ ከቄስ ማርቲን ሉተር ኪንግና ከሌሎቹ አያሌ

የሕዝባዊ የሠላም ትግል ሐዋርያት መረዳት ቀላል አይሆንም፡፡ የሕዝብን የሠላማዊ አመፅ ትግል የሚበግረው ተፃራሪ ኃይል ስለማይኖር ቀጣይና በማያባራ ሕዝባዊ አመፅ ወያኔን ማስወገድ ማለት በዘመናዊቷ ኢትዮጵያ ፥ ለሕዝባዊ ሠላማዊ አመፅ፥ አንድ አዲስ ከፍተኛ የታሪክ ምዕራፍ እንደማስመዝገብ ይቆጠራል፡፡ ይህ ደግሞ በወቅታዊው የዓለም ሁኔታ እየታየ ያለ ክስተት ሆኗል፡፡ ሰሞኑን በማዕከላዊው እስያ ሀገሮች የተፈፀመ ድርጊት ነው፡፡ ኢትዮጵያም የዓለም ኅብረተሰብ አባል እንደመሆኗ፥ ከዚህ ክስተት ልታመልጥ አትችልም፡፡ ሕዝቧም እንደ የካቲቱ 66 ሕዝባዊ አመፅ ሁሉ፥ ዛሬም እንደገና ያንኑ ሕዝባዊ ድል የሚጎናፀፍበት ወቅት ሩቅ አይሆንም፡፡

ደግመን ደጋግመን እንዳልነው፥ የሕዝብን ይትገል ስልት ወይም ምርጫ ወሳኝ ገዢው ኃይል ሊሆን አይችልም፡፡ታምፁና ወዮላችሁ ሲልም፥ ጭቆናህን ካላቆምክ ዋ መባል አለበት፡፡ ስለዚህም ሕዝብ መብቱን ለማስከበር ማመፅ መብቱ ነው፡፡ ከመብትም አልፎ ግዴታው ነው፡፡ ለመብቱና ለሰብዕናው መከበር፥ ያለአመፅ ሕዝብ ሁሌም በባርነትና በጭቆና ቀንበር ተቀይዶ ሲሰቃይ ይኖራል፡፡ አንገቱን ደፍቶ የሚገዛ ሕዝብ ሁሌም ሲጨቆን ይኖራል፤ሀገሩንም ሊያጣ ይችላል፡፡ ስለዚህ ማመፅ ግዴታ ነው፡፡ የመለስ አገዛዝ ለሕዝብ ጨኸት ጆሮ የሌለውና ሀገርን ሊያጠፋ የሚቅነዘነዝ ነው፡፡ ቢመክሩት አይሰማም፤ ቢለምኑት አይራራም፡፡ ጨካኝና ፀረ ሕዝብ ኃይል ነው የመንለውም ለዚሁ ነው፡፡ የወሮበላና የዱርዬ ጥርቅም ነው ስንልም ስድብ ሳይሆን፥ መሠረታዊ ዘቱን ለመጠቆም ነው፡፡ ይህ ህገወጥ ቡድን በሕዝብ አመፅ እንጂ፥ በሌላ መንገድ አይወገድም፡፡ የየክሬን፤የጆርጂያና ትላንትም የኪርጊስታን ተመክሮዎች መሳሌዎች ናቸው፡፡ ሕዝብ አምፆ ከተነሳ አገዛዙ የወረቀት ነብርነቱ ገሀድ ሆኖ ከትቢያ ይወድቃል፡፡ ስለዚህም በአገዛዙ ላይ ሆ ብሎ መነሳት ማመፅ የሕዝብ ወቅታዊና ለነገ የማይተላለፍ ግዴታ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ደጋግመን እንደምንለው፥ ሕዝብ በፈለገው መንገድ መታገል መብቱ ነው፡፡ ጭቆናን ለማስወገድ እስከፈለገ ድረስ! በሰለማዊ ሕዘባዊ አመፅ እንታገለላን የሚለው ምርጫ ብዙ ጉዳትን አስወግዶ ግን ከግብ ያደርሳል ተብሎ የተመረጠ እንጂ መስዋዕትን አይጠይቅም በሚል አይደለም፡፡ አንዳንድ የሠላም ትግል አባወራ ነን ብለው ብረት ያነሱትን ነጋ ጠባ የሚያወግዙ ግን፥ አንድ ቀን እንኳን የታሰሩ ይፈቱ ብለው ሲሰለፉ ያልታዩ፥ ሰላማዊ ትግልን በአፋዊ ደረጃ ሸብበው የትግልን ደብዛ ሊያጠፉ እንደሚጥሩ ታዝበናል፡፡ እነዚህ ቡድኖች፥ ሰልፋቸው በሀቅ ሲመረመር ከጨቋኙ ኃይል ጎን መሆኑ የሚረጋገጥ መሰሪዎች የሚሉት ሰላማዊ ትግል ማለትም ዝምታ እኛ ሠላማዊ ሕዝባዊ አመፅ ከምንለው በመሠረቱና በይዘቱ በጣም የተለየ ነው፡፡ እኛ ሠላማዊ ሕዝባዊ አመፅ ስንል፥ ሕዝብ ለመብቱ ሲል ማመፅ አለበት ለማለት ነው፡፡ ጥያቄው በዋና ደረጃ ፖለቲካዊ ነው፡፡ ሕዝብ፥ መብታችን ይከበር፤ የመለስ አገዛዝ ይወገድ ብሎ መሰለፍ፤ ማደም፤ መታገል ይገባዋል፡፡ የፖለቲካ ጥያቄ አይነሳ፤ አገዛዙ አትቆስቅሱት፤አታናዱት የሚሉት ክፍሎች የመለስ ዜናዊ ፀረ ትግል እሳት አደጋዎች፤እሳት አጥፌዎች ናቸው፡፡ ሰላማዊ ሕዝባዊ አመፁ አገዛዙ

ማናደድ አይደለም ብርክ አስይዞ ከሥልጣን ለማስወገድ የተቃኘ መሆን አለበት። ከአገዛዙ መተቃቀፍ ወይም ተቻችሎ መቀጠልን ሳይሆን አገዛዙ ማስወገድ መጣል ነው ዓላማው ሊሆን የሚችለው። በዚህ ላይ ብዥታ ሊኖር ከቶም አይገባም። ስለዚህም የማያቋረጥ የሕዝብን አመፅ-ትግል ማደራጀት የግድ ነው። የተቃውሞ ሰልፍ/ተፈቀደ አልተፈቀደ / ለፀረ ሕዝብ ህግ አንገዛም ማለት፤የሥራ ማቆም አድማ ማካሄድ፤ በአገዛዙ የ ግድ ተቋሞች ላይ ማዕቀብ ማድረግ፤ የረሀብ አድማ፤ሰልፍ፤ሰልፍ፤ሰልፍ፤የእምቢኝ አልገዛም አድማ አድማ አድማ-- ይህ ነው ፍቱኑ መንገድ አገዛዙ አስጨንቆ ለመጣልና ሀገርን ለማዳን። የኢሕአፓ መልዕክት ይህ ነው። ግልፅ ነው። የመለስ አገዛዝ በትግል ካልተወገደ ኢትዮጵያ ከጥፋት አትድንም፤ ህዝቧም መብቱን አያስከበርም የሚል ነው።